# <u>Learning by Ear 2013</u>

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 6: **«ምስጥሮች»**

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Daniel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**<u>INTRO/OUTRO:</u> NARRATOR**

**<u>SCENE 1: ዶክተር ዘሪሁን’S OFFICE</u>**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ዶክተር ዘሪሁን (M, 45)**

**<u>SCENE 2: AT THE POLICE STATION</u>**

- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

**<u>SCENE 3: THE አቶ ጃለታS LOOK FOR ንጉሴ</u>**

- **NEWS PRESENTER (F, 25)**
- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)**
- **ንጉሴ (M ,16)**

**<u>SCENE 4: ንጉሴ DRUNK AT HOME</u>**

- **ንጉሴ (M, 16)**
- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ዘውዲቱ(F, 35)**

## INTRO

### 1. NARRATOR:

**ጤና ይስጥልን አድማጮች! ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ  የሚቀርብላችሁ ተከታታይ ድራማ ነው።—«መዘዙን መቀበል»  የሚሰኘውየድራማው  ሁለተኛ ዙር ላይ እንገኛለን። እርግጠኛ ነኝ፤ የምህረት፣ ንጉሴ  እና የሌሎቹ ታሪክ እንዴት እንደሚቀጥል ለማወቅ ጓግታችኋል። ያቆምንበትን ለማስታወስ ያህል ንጉሴ የክፍሉ ተማሪ ምህረት እንደማትፈልገው ከነገረችው ወዲህ ሆኖ ከሚያውቀው በላይ መጥፎ ስሜት ውስጥ ነው ያለው። ባለፈው ጊዜ ከወላጆቹ ሳይቀር ተጣልቷል።:**

### 2. EPISODE 5, LINES 61 - 71:

*አቶ ጃለታ: (…)እናትህ እኮ እንደምን አደርክ ነው ያለችህ። እና ማለት የምትችለው« እንደሱ ካልሽ» ብቻ ነው?*

*ንጉሴ: እንግዲህ እሷ ጥሩ አድራ ይሆናል… ለኔ ግን ጥሩ አልነበረም። (…)*

***SFX: SLAP ON FACE***

*አቶ ጃለታ **(65):** ለእናትህ እንደዚህ አይነት መልስ አትስጥ! (…)*

***CUTLERY THROWN ON PLATE/**ንጉሴ **STANDS UP AND LEAVES***

*አቶ ጃለታ **(71):** ንጉሴ ና! ተመለስ ብያለሁ።….*

### 3. NARRATOR:

**በተመሳሳይ  አቶ ሙላቱ ከታሰሩ ጀምሮ የምህረት ቤተሰብ ኑሮን ያለረዳት  በመጋፈጥ ላይ ይገኛል። አባትየው በስርቆት ወንጀል ተጠርጥረው አሁንም ፖሊስ ጣቢያ ናቸው። ችግራቸው ይህ ብቻ አይደለም። ቀሪውን  በኋላ ላይ እንመለስበታለን።…**

ልጃቸው ምህረትም ችግር ውስጥ ትገኛለች። ከክፍል ጓደኛዋና በፍቅር እንደተሸነፈ ከነገራት ዳንኤል ጋ አብራ የግብረ ስጋ ግንኙነት ከፈፀመች በኋላ አርግዛለች። ለዳንኤል አንድ መፍትሄ ብቻ ነው የሚታየው፤ ፅንሱን ማስወረድ። የምህረት ጓደኛ ትዕግስትም ለምህረት የሰጠቻት ምክር ተመሳሳይ ነው። :

## 4. EPISODE 1, LINES 10 – 11:

*ትዕግስት: (…)ለማንኛውም አንቺ በቅርቡ መወሰን ያለብሽ ይመስለኛል። … ገባሽ…?*

*ምህረት: ትዕግስት ነገሩ አልተመቸኝም … ምን መሰለሽ። በዛ ላይ ዶ/ር ዘሪሁንን የምከፍለው ገንዘብ ከየት አገኛለሁ?*

ትዕግስት ለምን ይሆን ጓደኛዋ ምህረት ፅንሱን እስድታስወርድ የምትመክራት? በዛሬው « ምስጢሮች» በተሰኘው ጭውውት እንደርስበታለን። 6ኛው ክፍል ላይ እንገናለን።…

**<u>SCENE 1: ዶክተር ዘሪሁን’S OFFICE</u>**

## 5. ATMO: AT ዶክተር ዘሪሁን’S (INSIDE SHABBY SMALL HOUSE, TRAFFIC IN THE BACKGROUND)

**6.** ዶክተር ዘሪሁን: ትዕግስት ስራሽን ሳትሰሪ እየመጣሽ እኔን ገንዘብ ልትጠይቂ አትችይም።

**7.** ትዕግስት: ግን ዶክተር ዘሪሁን፤ ስራዬን እየሰራሁ እኮ ነው።

**8.** ዶክተር ዘሪሁን: ነው እንዴ? ለመጨረሻ ጊዜ ደንበኛ ያመጣሽልኝ መቼ እንደነበር ታውቂያለሽ? ከሶስት ወራት በፊት።

**9.** ትዕግስት: የጠየኩዎት እኮ በጣም ትንሽ ገንዘብ ነው ዶክተር ዘሪሁን! እነዛን አዳዲስ ጫማዎች ለ መግዛት በጣም ጓጉቼያለሁ።

**10.** ዶክተር ዘሪሁን: አዝናለሁ ትዕግስት። ውል፤ ውል ነው። የተስማማነው ፅንስ ማስወረድ የሚፈልጉ ወጣት ሴት ልጆችን ስታመጪልኝ እንደምከፍልሽ ነው። ያለ ሴት ልጆቹ– ገንዘብ የለም።

**11.** ትዕግስት: አባክዎን ዶክተር ዘሪሁን …

**12.** ዶክተር ዘሪሁን: **(sighs)** አንድ ነገር ልንገርሽ ትዕግስት። ያቺ ያንቺን ጓደኛ አሳምነሽ ካመጣሻት.... ማን ነበር ስሟ – ምህረት? – በአሁኑ የበለጠ ጭማሪ እከፍልሻለሁ። ተስማማን?

**13.** ትዕግስት: ግን አሁን ገንዘቡ ያስፈልገኛል!

***KW BEGIN***

**14.** ዶክተር ዘሪሁን: ትዕግስት ትዕግስት! ሲያዩሽ ደሀ አትመስይም።... እነሱን ጫማዎች ለምን እናትሽ አትገዛልሽም?

**15.** ትዕግስት: **(impatient)** ነገርኩዎት እኮ! እናቴ በአሁን ሰዓት እቤት የለችም። ሌላ ጥያቄ አልዎ ወይንስ ገንዘቡን ይሰጡኛል?

**16.** ዶክተር ዘሪሁን: **(slimy)** እንግዲህ። እናትሽ እቤት ከሌለች እና ብቸኝነት የሚሰማሽ ከሆነ ወደእኔ ቤት ሁሌ ብትመጪ በሩ ክፍት ነው። እና ምን ማድረግ እንደምንችል እናያለን።

**17.** ትዕግስት: **(annoyed)** አይ አመሰግናለሁ! እቤትዎ የሚመጡትን ሴት ልጆች ምን እንደሚያደርጓቸው የማላውቅ መሰልዎ?ሊረዱኝ ካልፈለጉ እንደዛ ይበሉ።

***KW END***

**18. SFX: STEPS** ትዕግስት **GOING AWAY**

**19.** ዶክተር ዘሪሁን: ትዕግስት ቆይኝ!

**20. SFX: FOOTSTEPS STOP**

**21. SFX: BILLS BEING COUNTED**

**22.** ዶክተር ዘሪሁን: ጥሩ! – 20 ዶላር ይሄውልሽ። ቀጥሎ ከሚከፈልሽ አበል ላይ እቆርጠዋለው እሺ?

**23. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 2: AT THE POLICE STATION</u>**

**24. ATMO: INSIDE THE POLICE STATION, VISITING AREA**

**25. SFX: STEEL DOOR OPENS IN BACKGROUND**

**26. SFX: STEPS -** አቶ ሙላቱ **APPROACHES**

**27.** አቶ ሙላቱ: ሉሊት፤ ባለቤቴ! ልጠይቂኝ ስለመጣሽ አመሰግናለሁ። እስቲ እቀፊኝ። ፖሊስ ጣቢያ መታሰር ምን ማለት እንደሆነ ልታውቂ አትችይም። …

**28.** ወ/ሮ ሉሊት: **(stern)** ትንሽ እንኳን አታስብም። አትንካኝ። እንስሳ!

**29.** አቶ ሙላቱ: እንዴ ምን አደረኩ?

**30.** ወ/ሮ ሉሊት: እ! አሁን ጨርሶ እንደማያውቅ ትሆናለህ። አግኝቻታለሁ። ሙላቱ። ልጄን አግኝቼያታለሁ!

**31.** አቶ ሙላቱ: ምህረትን? ጠፍታ ነበር እንዴ?

**32.** ወ/ሮ ሉሊት: ምህረትን አይደለም! የሸጥካትን ነው እንጂ! ከወራት በፊት የወለድኳት ትንሽዋን ልጄን። ለዛ ለመኩሪያ የሸጥካትን !

**33.** አቶ ሙላቱ: **(angry)**ምንም አይነት ጥያቄ እንዳትጠይቂው ብዬሽ ነበር!

**34.** ወ/ሮ ሉሊት: አትደርስበትም ብለህ ነበር? ደግሞ እንድታውቀው ያህል ፤ ይህንንም ለፖሊስ አመልክቼያለሁ። እነሱም ጉዳዩን እየተከታተልን ነው ብለውኛል።

***KW BEGIN***

**35.** አቶ ሙላቱ: **(ironically)** እሺ በጣም አመሰግናለሁ። በእውነት አመሰግናከሁ ፤ ሉሊት። እቅድሽ ሰምሯል። ህይወቴን ምስቅልቅሉን አወጣሽው። ድሮም አውቀው ነበር። ሀብቴን ብቻሽን ልትደሰችበት እኔን ወደጎን ትይ ነበር።

**36.** ወ/ሮ ሉሊት: **(snaps)** የትኛውን ሀብት ሙላቱ?

***KW END***

**37.** አቶ ሙላቱ: ወህኒ ቤት ላክሽኝ ሉሊት።

**38.** ወ/ሮ ሉሊት: ትክክለኛው ቦታህ ነው ያለኸው። እስር ቤት! ልጆችህ ላቦሪያ ሳሉ የገጠማቸውን ሰቆቃ ታውቃለህ? ሁሉንም ነገር ነግረውኛል። እህትህ በፍፁም አልተንከባከበቻቸውም። በቀጥታ ወደ ማዕድን ማውጫ ነው የላከቻቸው— እዛ ጨለማ ጉድጓድ ውስጥ። ተቆጣጣሪው ይደበድባቸው ነበር። ምስኪን ልጆቼ። ከመጡ ጀምሮ ቅዱስ ሳይቃዥ ያደረበት አንድ ለሊት እንኳን የለም።

**39.** አቶ ሙላቱ: ሉሊት የኔ ውድ– ስራ ሳይኖርሽ ቤተሰብሽን ብቻሽን ማስተዳደር እንዴት ከባድ እንደሆነ ስለማታውቂው ነው። እና --

**40.** ወ/ሮ ሉሊት: **(angrily)** እና መፍትሄው ልጆችህን አሳልፈህ መስጠት ነው? መሸጥ? ልጄ አብራኝ እንድትሆን ፈልጌ ነበር። አንተ ግን ከኔ ነጥቀህ ወሰድክብኝ። አሁን ያለችበትን እስካወኩ ድረስ እንድትመለስልኝ የተቻለኝን በሙሉ አደርጋለሁ። እዛው እስር ቤት በበሰበስክ!

**41. SFX: STANDS UP AND LEAVES**

**42. SFX: STEPS ወ/ሮ ሉሊት GOING AWAY**

**43.** አቶ ሙላቱ: መቼ ነው ተመልሰሽ የምትመጪው?

**44.** ወ/ሮ ሉሊት: **(calls from far)** መቼም!

**45. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 3: THE አቶ ጃለታS LOOK FOR ንጉሴ

**46. SFX: CAR STARTED (HEARD FROM INSIDE)**

**47. SFX: ATMO INSIDE DRIVING CAR (አቶ ጃለታ’S CAR)**

**48.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(panicking)** ንጉሴ የት ሊሆን ይችላል? ስልኩን አይመልስም። ጎረቤቶቹም አላዩትም። …

**49.** አቶ ጃለታ፡ ተረጋጊ የንጉሴ እናት። ልጃችንን እናገኘዋለን። ወደ መሀል ከተማ እንንዳ እና እዛ እንፈልገው።....

**50.** ወ/ሮ ዘውዲቱ፡ እንዴት ነው እንድረጋጋ የምትፈልገው። ከምሽቱ 4 ሰዓት ሆኗል ፤ንጉሴ ዛሬ ጠዋት ከተጣላችሁ ጀምሮ ወደ ቤት አልተመለሰም።

**51.** አቶ ጃለታ፡ **(angry)** ነግሬሻለሁ እኔን መውቀስሽን ተይ። እናገኘዋለን።

**SILENCE** ***KW BEGIN***

**52. SFX: CAR RADIO IS TURNED ON**

**53. NEWS PRESENTER:** በጎረቤት ሀገር ላቦሪያ የመፈንቅለ መንግስቱ ሂደቱ አስጊ ሁኔታ ላይ መድረሱ ዓለም እያሳሰበ ይገኛል። የገዢው መንግስት ተቃዋሚዎች  የኃይል ርምጃ እየወሰዱ ይገኛሉ።  እንደ ዜና ምንጮቻችን ከሆነ አማፂያኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ ብቻ አይደለም ጥቃት እያደረሱ ያሉት። የካሳሁን ማዕድን ድርጅትን ጨምሮ የተለያዩ ማዕድን ማውጫዎች ላይ ጥቃት ደርሷል። እስካሁን የሞቱት ሰዎች ቁጥር ቢያንስ 10 እንደሚደርስ እና ከነዚህም ውስጥ በወቅቱ በካሳሁን ማዕድን ድርጅት ውስጥ በህገ ወጥ መንገድ ይሰሩ የነበሩ ህፃናት ልጆች ይገኙበታል። የማዕድን ማውጫው ባለቤት የሆኑት አቶ አያና ካሳሁን ለመንግስት ባለስልጣናት ቅርብ እንደሆኑ እና ላለፉት ቀናት በከተማው እንዳልታዩ ነው የሚነገረው።

**(radio continues under conversation)** አሁን ደግሞ የአይር ትንበያ ዘገባ ይኖረናል ።በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚጥለው ከፍተኛ ዝናብ ለከተማ ነዋሪዎች የማያስደስት ዜና ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ባሁኑ ጥሩ ምርት ለሚጠብቁትን ገበሬዎች አስደሳች ዜና ነው።።...

**54.** አቶ ጃለታ: የንጉሴ እናት … ይህንን አቶ ካሳሁን የሚል ስም ከዚህ በፊት ሰምቼው የማውቅ መሰለኝ።

**55. SFX: RADIO TURNED OFF**

**56.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(angry)** ልጃችን ጠፍቶ ዜና እንዴት እሺ ብሎ ይሰማልሀል?

***KW END***

**57.** አቶ ጃለታ: **(deep breath)** ምናልባት ከሆነች ልጅ ጋ ሊዝናና ሄዶ ይሆናል የጠፋው።

**58.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: እንዴት እንዲህ ትላለህ? ንጉሴ ገና ተማሪ ነው! **(suddenly)** አቁም! አየኸው?

**59.** አቶ ጃለታ: ምኑን?

**60. SFX: CAR BRAKES**

**61.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: እዛ ጋ የሆነ ሰው ጓዳና ላይ ተኝቷል። ተጎድቶ  እና ምናልባት ርዳታ ሊያስፈልገው ይችላል።…

**62. SFX: CAR GOES BACK**

**63.** አቶ ጃለታ: ምንም ያየሁት ነገር የለም…ስሚ መኪና ውስጥ ብንቆይ እና ፖሊስ ብንጠራ ይሻላል። ምናልባት ሌቦች ሊያታልሉን ያጠመዱት ወጥመድ ነው።

**64. SFX: CAR  STOPS**

**65.** አቶ ጃለታ: **(short pause while he observes)** … እረቶይ … እውነትሽን ነው መንገዱ ላይ የሆነ ሰው ወድቋል። … የፌጣሪ ያለ ንጉሴን ይመስላል።

**66.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(worried)** ምን? ጌታዬ ሆይ። አደራህን ። ልጄ ብቻ እንዳይሆን!

**67. SFX: TWO CAR DOORS OPENS,** አቶ ጃለታ**S GET OUT, FEW FOOTSTEPS ON GRAVEL (TWO PERSONS)**

**68. SFX: ATMO STREET SOUNDS, QUIET NEIGHBOUROOD, CRICKETS**

**69.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ደህና ይሆን? ንጉሴ!

**70.** አቶ ጃለታ: ንጉሴ? ተጎድተሀል?

**71.** ንጉሴ: **(drunk)** እኔ? ልጎዳ? በፍፁም! ሀይለኛውን ንጉሴን ማንም ሊጎዳ አይችልም!

**72.** አቶ ጃለታ: ሰክርሀል እንዴ? **(angry)** አንተ ልጅ ምን ሆነሀል?

**73.** ንጉሴ: ልጅህ ከሆነች ልጅ ፍቅር ይዞታል። ልጅቷ ግን ሌላ ሰው ነው የምታፈቅረው ይህ ነው የሆነው።

**74.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ንጉሴ! ምን እየሆንክ ነው?

**75.** አቶ ጃለታ: ከሰከረ ጋ እያወራሽ ጊዜሽን እያቃጠልሽ ነው። ይልቁንስ መኪና ውስጥ እናስገባው። እርጂኝ።

**76. MR. &** ወ/ሮ ዘውዲቱ**PANT AS THEY LIFT** ንጉሴ **UP**

**77.** ንጉሴ: **(sings and laughs)** አዎ! ወደቤቴ ውሰዱኝ!

**78.** አቶ ጃለታ: **(more to himself)** እዛ እስከምንደርስ ጠብቅ ብቻ…

**79. SFX: CAR DOOR OPENED**

**80. SFX: CLOTH RUSTLE AS ንጉሴ IS PUT INSIDE**

**81. SFX: CAR DOOR CLOSED**

**82. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 4: ንጉሴ DRUNK AT HOME**

**83. ATMO: AT THE አቶ ጃለታS’, AT NIGHT**

**84.** ንጉሴ: **(pukes)**

**85. SFX: SOUND OF PUKING INTO A BUCKET**

**86.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(worried)** ኡ! ንጉሴ እንዴት እንደዚህ ብዙ ትጠጣለህ?

**87.** አቶ ጃለታ: ቆይኝ እረ እኔ እጠይቀዋለሁ። ንጉሴ – እንደዚህ አይነት አመል ምን የሚሉት ነው?

**88.** ንጉሴ: አባዬ --

**89. SFX: SLAP ON THE ARM**

**90.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: አትምታው እንጂ ጃለታ!

**91.** አቶ ጃለታ: ልጄ ነው። የፈለሁትን ያህል ልመታው እችላለሁ።

**92.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ግን የምታደርገው ነገር ምንም አይበጅም።በቅርቡ ብቻ ስንት ጊዜ መተኸዋል?

**93.** አቶ ጃለታ: **(sarcastic)** እና ምን ብናደርግ ይሻላል ትያለሽ የእኛ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ?

**94.** ንጉሴ: **(pukes)**

**95.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(firmly)** እኔ የምመክርህ አረጋ ማለቱን ነው። ከሰከረ ሰው ጋ አሁን መወያየት አትችልም። አረፍ ይበልና ነገ ስካሩ ሲለቀው ታናግረዋለህ።

***KW BEGIN***

**96.** አቶ ጃለታ: **(disgusted)** መነጋገር ከአለበት ሁኔታ አይመልሰውም።

**97.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(thoughtful)** ጃለታ ፤ እውነቴን ነው የምልህ ትክክል እየሰራን አይመስለኝም። ምናልባት ከሱ ጋ ጓደኛ መሆን ብንሞክር አይሻልም ትላለህ?

**98.** ንጉሴ: **(mumbles to himself)** ጓደኛ... ጓደኞች አያስፈልጉኝም። ምህረትን ነው የምፈልገው...

**99.** አቶ ጃለታ: አፍህን ዝጋና ገብተህ ተኛ።

***KW END***

## 100. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>

**እንግዲህ ንጉሴን በማግስቱ ለሚጠብቀው የዞረ ድምር ትተነው እዚህ ላይ የዛሬውን «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» የሚለውን የበማድመጥ መማር ጭውውት እናበቃለን። ንጉሴ የገጠሙትን ችግሮች መቋቋም ይችል ይሆን? ምህረትስ? ልጁን ለመውለድ ወይንም ፅንሱን ለማስወረድ ምን ውሳኔ ላይ ትደርስ ይሆን? የሚቀጥለው የጭውውት ክፍል እንዳያመልጣችሁ እርግጠኛ ሁኑ። ስለዚህ ዝግጅት የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከፈለጋችሁ** dw.de/lbe **የሚለውን ድረ ገፅ ጎብኙ። በፌስ ቡክ ገፃችን ላይ ገብታችሁ ከሌሎች ጋ ስለአዳመጣችሁት ልትወያዩም እንደምትችሉ ለማስታወስ እንወዳለን። ጤና ይስጥልን።**